መጋቢት 26 ቀን 2005 ዓ.ም.

# የቆራሄ ጀግና አፈወርቅ ወልደ ሰማያት የፋሺስት ኢጣሊያን ጦር የመከተ

ከዓለማየሁ አበበ ሽንቁጥ
( የቀድሞ አምባሳደር)

ቤኒቶ ሙሶሊኒ ሐሙስ ማታ በ12 ሰዓት ላይ መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም. ከጽሕፈት ቤቱ ሰገነት ብቅ ብሎ በመቆም ንግግሩን ለመስማት ይጠባበቅ ለነበረው ለመላው የጣሊያን ሕዝብ "ኢትዮጵያን ለ40 ዓመታት ታገስናት እንግዴህስ በቃ" ብሎ ረጅም የድንፋት ንግግር ሲያደርግ የሕዝቡ ደስታ እጅግ በጋለ መልኩ ይስተጋባ ነበር::ይህም በተንቀሳቃሽ የፊልም ምስል በዓለም ዙሪያ ታይቱዋል፡፡ ለአገራቸው ተቆርቁዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን በቁጭጥትና በንዴት ይመለከቱታል፡፡

የሙሶሎኒ ንግግር ከመሰማቱ ሰባት ሰዓት ቀደም ብሎ መስከረም 21 ቀን 1928 ዓ.ም. እኩለ ቀን ሲሆን ፋሺስቱ ጄ.ደ. ቦኖ ከመረብ ወንዝ 50 ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ለወረራ ሲዘጋጅ ነበር:: ከንጋቱ 11 ሰዓት ሲሆን: 268000 የጦር ወታደር:7000 መኮንኖች:150 ታንኮች:150 አዳኝና ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች:700 ልዩ ልዩ መድፎች:6000 ከባድና ቀላል መትረየሶች:6000 የጭነት ከብቶች:2300 ተሽከርካሪዎች ይዞ በመንቀሳቀስ ከጧቱ 3 ሰዓት ተኩል ሲሆን መረብን ተሻግሮ ወደ ኢትዮጵያ ዘለቀ:: መረብን ሲሻገር የኢትዮጵያ ጦር በሚወስደው የመከላከልና የማጥቃት እርምጃ ችግር ይፈጥርብኛል ብሎ የነበረው የጠላት ጦር ስጋቱ እውን ሳይሆን ያለአንዳች ተቃውሞ ሰተት በሎ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ገባ::

ጣሊያኖች በወረሩበት ዋዜማ መስከረም 21 ቀን ቀዳማዊ ሀይለ ሥላሴ የእንጦጦ ማርያምን አንግሰው በማግስቱ መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም. የክተት አዋጅ ተነቦ ነጋሪት ተጎስሞ ነበር::

ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ የዘመቱበት ሰበብ በብዙ መላምቶች ሊታጀብ ቢችልም ዋናውና ትልቁ ምክንያት ግን በዘመናዊ የዓለም ታሪክ ጥቁር ሕዝብ አንድን የአውሮፓ ሀይል አዋርዶ ያባረረውን ታሪክ ለማደስ የተጠነሰሰ እንደነበር መገመትና ማመን አያዳግትም::

ጣሊያኖች ለጦርነት 40 ዓመት ሲዘጋጁ ኢትዮጵያ ለጦርነት ዝግጅት ያደረገችው 3 ዓመት ከጦርነቱ መፈንዳት በፊት እንደነበር የታሪክ ተመራማሪዎች ይመሰክራሉ :: ራስ ሙሉጌታ በወቅቱ የኢትዮጵያ የጦር ሚኒስትር የነበሩት በታህሣስ ወር 1927(ዲሴምበር ወር 1934) ኢትዮጵያ የነበራት አንድ ሚሊዮን በአብዛኛው ዘመን ያለፈባቸው ጠብመንጃዎችና ወደ

150 ሚሊዮን የሚጠጋ ጥይቶች እንደነበር መግለጣቸው ይታወቃል:: የጦርነቱ ጊዜ እየተቃረበ በሄደበት ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት ዘመናዊ መሣሪያዎችን ለመግዛዛት በነፍስ ወከፍ አንዳንድ ብር ሕዝቡ እንዲያዋጣ የመንግስት ሠራተኛ ከደመወዙ ሃያ በመቶ እንዲያዋጡ በማድረግ የተገኘውን ያህል ተሰብስቦ እንዲሁም የአገሪቱ ሀብት ከቻለው ሁሉ ተጠራቅሞ ግዢው ሲፈፀም ጣሊያኖችን አስግቷቸው ነበር:: አንዳንድ ዘመናዊ መሣሪያዎችም ከቼኮስሎቫኪያ ከቤጀምና ከጀርመን በጂቡቲ በኩል አዲስ አበባ ሲደርሱ ንጉሠ ነገሥቱ እራሳቸው ባቡር ጣቢያ በመሄድ የመጣውን በጉጉት ይመለከቱ ነበር:: አንዳንድ ክፍያቸው ተፈፅሞ የነበረ መሣሪያዎች ወደ ኢትዮጵያ ሊገቡ በጭነት ላይ እያሉ "ሊግ ኦፍ ኔሽንስ" የዘመኑ የዓለም መንግሥታት ማህብር በኢትዮጵያና በጣሊያን ላይ የጦር መሣሪያን ግዢን ስላገደ ለኢትዮጵያ የሚገቡት መሣሪያዎች ሁሉ ጂቡቲ ሲደርሱ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ የፈረንሳይ መንግስት አግዶት ነበር:: ጣሊያን ግን ቀደም ሲል ካስገባችውና በምታመርታቸው መሣሪያዎች ጦሯን በማስታጠቋ እገዳው አልጎዳትም ነበር::

በዘመናዊ የጦር ስልት ይከላከላሉ ተብሎ ተስፋ የተጣለባቸው በሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ገብተው የሰለጠኑ ጥቂት ሠልጣኞች ነበሩ:: ግርማዊ ቀዳማዊ ሀይለ ሥላሴ በተገኙበት መጋቢት 7 ቀን 1927 ዓ ም በዘመናዊ መሣሪያ ታጥቀው በጃንሜዳ ሰልፍ ያሳዩት 3000 የሚሆኑ መኮንኖችና ወታደሮች ነበሩ:: ስለሆነም ለ 40 ዓመታት በጦር ሀይል ተዘጋጅቶ ለመጣ ሠራዊት የሚከላከል ሃይል አለመዘጋጀቱ አል አይባልም፡፡

መስከረም 23 ቀን 1928 ዓም ( እ.አ.እ. ኦክቶበር 3 ቀን 1935 ዓ. ም. መሆኑ ነው ) ጣሊያኖች የሰሜን ኢትዮጵያን ወሰን ጥሰው ሲገቡ ኢትዮጵያ ለጦርነት ዝግጁ እንዳልነበረች አመልካቹ አንድም የመከላከያ ሀይል በአካባቢው ዘርግታ የመከላከል ተግባር አለመፈፀሟ ነው :: ጣሊያን በኤርትራም ሆነ በጣሊያን ሱማሌላነድ በኩል የምታደርገው መሰናዶ እየታወቀ በመረብ በኩል ከኢትዮጵያ በኩል አንዳችም ማስፈራሪያ ሳይደርስባት ጣሊያን ወታደረቿን ሰተት አድርጋ ማስገባቷ ሁሉንም አስገርሟል::

በኦጋዴን በኩል ጣሊያኖች የቀየሱት እቅድ የሚላን ፕላን የተሰኘ ነበር:: እቅዱ በሦስት የተከፈለ እንደነበር ይታወቃል:: እነሱም ምዕራብ መሃልና ምሥራቅ የተሰኙ ነበር::



1. የምዕራብ ጦር ግምባር የኢትዮጵያ ጠረፍ ከተማ የሆኑትን ዶሎንና አካባቢዋን ለመያዝ ነበር:: የዚህ ጦር አዛዥ ኮሎኔል ሚሼሊ ይባል ነበር:: የሚሼሊ ጦር አክቶበር 4 ቀን 1935 (ጥቅምት11 ቀን 1928 ዓ.ም.) በቀኑ 11 ሰዓት ላይ ጦርነት ከፍቶ ወዲያውኑ ጣሊያኖች አካባቢውን በቁጥጥራቸው ሥር አዋሉት::

ይህ ጦርነት ሲከፈት ግራዝማች መኩሪያ ተሰማ የተባሉት የጠረፍ ጥበቃው አዛዥ በጀግንነት ተዋግተው ብዙ ቦታ ቆስለው እጄን ለጠላት አልሰጥም ብለው በጩካኙ የጠላት ጦር ተሰውተዋል፡፡አካባቢውም በጣሊያኖች ቁጥጥር ሥር እንደዋለ የግራዝማች መኩሪያን ጀግንነት ጠላትም ስለተገነዘበ በክብር እንዲቀበሩ አድርጉዋል::

2. ሁለተኛው ዕቅድ በመሃል ግንባር ተሰልፎ የሚጠባበቀውን ጦር በማሰማራት የዋቢ ሸበሌን ሜዳማ መሬት ለመያዝ ነበር:: ይህም በጄኔራል ፍሩሽ የሚመራው ጦር ነበር፡፡ የጣሊያኑ ጦር በጦር አውሮፕላኖች እይተረዳ በኦክቶበር 18 ቀን 1935 ዓ.ም.( ጥቅምት15 ቀን 1928 ዓ.ም. ቀላፎን ሺላቦን ለመያዝ ቻለ::በኢትዮጵያ በኩል የጠረፉ ጦር አዛዥ የነበሩት ግራዝማች በላቸው የተባሉ ጀግና እጃቸውን ሳይሰጡ በጀግንነት ተዋግተው በጩካኙ የጠላት ጦር ተሰውተዋል::

3. በምሥራቅ በኩል የተሰማራው የጣሊያን ጦር የሚመራው በኮሎኔል ማሊቲ ነበር:: በኢትዮጵያ በኩል ቆራሄንና አካባቢውን በአስተዳዳሪነትና በጠረፌ ጠባቂነት የተመደቡት ግራዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማያት ነበሩ::

በኦጋደን የሠፈሩ የኢትዮጵያ ጠረፍ ጠባቂ ወታደሮች የጣሊያን ጦር ጥሶ ሲገባ በአስቸኳይ እርዳታ የሚያገኙበት ዕድል አልነበራቸውም:: እዚያው በእጃቸው በሚገኘው ሀይል ተጠቅመው መከላከል ነበረባቸው ጄ ፍሩሽ ( G. L. Frusci) በመጽሐፋቸው እንደገለጡት ፡: በየጣቢያው የሠፈሩት የኢትዮጵያ የጠረፍ ጠባቂዎች ቁጥር እጅግ በጣም አነስተኛ ነበር:: ምንም እንኳን ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም በላያቸውም ላይ የሚወርደው የጥይትና የቦምብ ናዳ አስደንጋጭ ቢሆንም በወረራውና በሃይሉ ሳይደናገጡ በጣሊያኖችን ከፍተኛ የሀይል መጠን ያልጠበቁቀ ዓይነት ቢሆንም ወረራውን በሀይልና በወኔ ተቋቁመውታል::

አፈወርቅ ወልድ ሰማያት ከመምህር ወልደሰማያት በ1898 ዓ ም አቃቂ በሰቃ በተባለ ሥፍራ ተወለዱ:: የአማርኛ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ምስለኔ ከዚያም የጂጂጋ አውራጃ ዲሬክተር ሆነው ሠርተዋል::አቶ አፈወርቅ ገና በጎልማሳ እድሜያቸው ክብርት ወይዘሮ ተዋበች ካሴን አግብተው አምስት ልጆችን ወልደው ነበር ሦስቱ በልጅነት እድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ሻለቃ ጌታቸው አፈወርቅ የክብር ዘበኛ ሠራዊት መኮንን በመሆን

አገራቸውን በቅንነት አገልግለው በጡረታ ላይ እንዳሉ በደረባቸው ሕመም ምክንያት ከዚህ ዓለም ተለይተዋል:: ትንሹ ልጃቸው አቶ ሀይሉ አፈወርቅ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በተለያዩ አገሮች በዲፕሎማትንት አገራቸውን አገልግለው በጡረታ ላይ እንዳሉ በደረሰባቸው ህመም ምክንያት በአገር ቤትም ሆነ በውጭ አገር ህክማና ሲደረግላቸው ቆይተው መጋቢት 8 ቀን 2001 ዓ.ም. በተወለዱ በ78 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡

አቶ አፈወርቅ ከወልወል ጦርነት በኋላ በቆራሂና በገርለጎቤ ከአንድ ዓመት በላይ መሽገው የጠላትን ሰርጎ ገቦች በብቃት በመከላከላቸው ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው የግራዝማችነት ሹመት የተሰጣቸው ቆፍጣና የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ ነበሩ::

በቆራሂ የግራዝማች አፈወርቅ ምሽግ ዘመናዊ ነው ባይባልም የአይን ምሥክሮች እንዳረጋገጡት ያለምንም ርህራሄ ከላይ ከአውሮፕላን ለሚዘንበው ቦምብ በቂ መከላከያ ነበር:: በየምሽጎቹ ወደ 1500 የሚሆኑ ወታደሮች ይሸሽጉ እንደነበር በታሪክ ተዘግቧል::

ግራዝማች አፈወርቅ በቆራሂ አስተዳዳሪና የጦር አዝመች ብቻ አልነበሩም የጦር ሜዳው ግምባር ቀደም ተዋጊም እንደነበሩም አስመስክረዋል:: የጠላት አውሮፕላን ከሩቅ ቦታ ሆኖ ቦምብ ቢወረውር የአውሮፕላን መከላከያ ይዘው ከሩቁ ሆነው ብቸኛዋን ኦርሊኮኑን (Oerloikon) የሚተኩሱ እሳቸው ብቻ የሚተኩሱት በመሆናቸው እራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ጠላትን የተፋለሙ ጀግና ነበሩ::በአካባቢውም የአውሮፕላን ማውረጃ መሣሪያ ይኸው አንዱ ኦርሊኮን ብቻ ነበር::

ጥቅምት 6 ቀን 1928 ዓ.ም. የጠላት አውሮፕላን ቦምብ እንደዝናብ ሲያወርድባቸው አፈወርቅ ኦረኒኮኑን በመተኮስ አውሮፕላኖቹን ሲያባርሩ እንደነበር እንግሊዛዊው ጋዜጠኛ ስቲር(G. L. STEER) የተባለው የምሥክር ቃሉን ሰጥቷል:: የግራዝማች አፈወርቅ የመከላከል አቅም ጣሊያኖችን ስላስገረማቸው የጣሊያን ፀሐፊዎች ግራዝማች አፈወርቅ 60 የሚጠጉ ፀረ ታንክና መትረየሶች ነበራቸው ብለው ቢጽፉም እውነታው ከላይ የተጠቀሱት የዓይን ምሥክር ጋዜጠኛ እንደገለጡት ከአንድ ኦርሊኮንና ከአራት ሌሎች ዘመናዊ መሣሪያዎች በስተቀር ሌሎቹ መሣሪዎቻቸው ግን ዘመን ያለፈባቸው እንደነበረሩ ተገልጧል::

የጣሊያን ጦር መሪዎች በግራዝማቹ ላይ እና በአካባቢው ያዘመቱት ግን ስድስት ባታሊዮን ጦር:150 ተሽከርካሪዎች: 9 ታንኮች: 20 ብረት ለበስ መኪናዎች እንደነበሩ ተዘግቧል::

ይህን የተከማቸና የዳበረ የጣሊያን ሀይል መኖሩን አፈወርቅ ቀደም ብለው በስለላ ከደረሱበት በኋላ ተጨማሪ ጦር ከዘመናዊ የጦር መሣሪያ ጋር እንዲላክላቸው ጠይቀው ልዩነት ሊያመጣ የሚችል ባይሆንም 600 የሚሆኑ ተጨማሪ ወታደሮች ተልኮላቸዋል::የተላከላቸው ሀይል ቀድሞ ከነበረው ሀይል ጋር ተዳምሮም ጣሊያን ያሠለፈውን ጦር ሊመክት የሚችል አልነበረም::

ጥቅምት 23ቀን 1928 ዓ.ም. ሀያ የሆኑ የጠላት አውሮፕላኖች ቦምባቸውን ማዝነብ ጀመሩ::እነዚህን አውሮፕላኖች ከአካባቢው ለማባረር አፈወርቅ የወሰደባቸው ጊዜ 30 ደቂቃ ብቻ ነበረ ሲል ስትር ምሥክርነቱን ሠጥቷል:: ይህ ሁሉ ሲሆን አፈወርቅ በወታደሮቻቸው መሀል እየተዘዋወሩ የወታደሩን መንፈስ የሚያነቃቃ ንግግር ያደርጉ ነበር <u>**"አብረን እንድበላን አብረን እንሞታለን እንጂ እኔን ጥለህ የት ትሄዳለህ ?በሠላሙ ቀን ከወደድከኝ በዚች ቀውጢ ቀን ብቻዬን ጥለህ የት ትሄዳለህ ብቻዬን ጥለኸኝ እንደማትሄድ አውቃለሁ:: እንደምትወዱኝ እወዳችኋለሁ:: በሠላሙ ጊዜ ጭብጦና በሶ ተካፍለን በልተን አሁን እንዴት ይርበናል:: ስንቄን አካፍዬ እንዳበላሁህ የመከራየዬም ተካፋይ ሁነኝ::አፈወርቅ እጁን ለጠላት አይሰጥም አንተ የአፈወርቅ ነህና የተቀደሰ እጅህን ላልተቀደሰ ጠላት እጅህን አትሰጥም"**</u> እያሉ የተለመደ ንግግራቸውን ለወታደሮቻቸው ያሰሙ ነበር::

ጥቅምት 23 ቀን በአንድ በተጣለ ቦምድ አፈወርቅ ቅልጥማቸውንና ቁርጪምጭማቸው ላይ ክፉኛ ቆሰሉ:: አፈወርቅ መንፈሰ ጠንካራና የማይበገር ፅናት ስለነበራቸው ከዓላማቸው የማይንቀሳቀሱ ነበሩ:: ስለሆነም ይህን ከባድ የሆነ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸው ለመታከም ወደ ደጋሀቡር በመሄድ በቀይ መስቀል የሕክምና ማዕከል እርዳታ ባገኙ ነበር :: እሳቸው ይህን ቢያደርጉ ጦራቸው የመበተን አደጋ ይደርስበታል ብለው በመስጋት ነበር **"ይህን ምሽግ ጥለን አንሄድም መቀበሪያችን ይሆናል እንጂ"** በማለት የሠራዊታቸውን መንፈስ ያነቃቁም ያደፋፍሩም ነበር::

ጥቅምት 24 ቀን 1928 ዓ.ም. በግራዝማች አፈወርቅ የጦር ሠፈርና በአካባቢው የአውሮፕላኑ ድብደባው በተጠናከር መልኩ ቀጥሎ ዋለ::በጣሊያን አውሮፕላን በተጣለ ቦምብ የደረሰባቸው ከባድ የመቁስል አደጋ እነደልባቸው እነዳይንቀሳቀሱ ገደባቸው፡፡ ሆኖም ኅበዙ ጀግና ቁስላቸውን ጠጋግነው ወታደሮቻቸውን ከማበረታታና የአውሮፕላኑን ጥቃት ከመከላከል አልቦዘኑም ነበር::

የግራዝማች አፈወርቅን ምሽግ ለመያዝ ከአውሮፕላኑ ድብደባ በተጨማሪ: የአረብና የሱማሌ የጦር ቡድኖች:የባንዳ ቡድን:አንድ ባታሊዮን የጣሊያን እግረኛ:የታንክ ቡድን ወደ ቆራሄ በግስጋሴ ላይ ነበር:

ጥቅምት 25 ቀን 1928 ዓ.ም. ዕለት ግራዝማች አፈወርቅ ቁስላቸውን ስላላስታመሙት ቁስሉ እየጠና አካላቸው እየዛለ ሄዶ የጠላትን አውሮፕላን

ከሚያሸብሩበት ኦርሊኮናቸው ላይ ወደቁ ::   የኦርሊኮኑ ድምፅ እንዳቆመ አፈወርቅ መሞታቸው በሠራዊታቸውና በነዋሪው ሕዝብ ዘንድ ታወቀ ብሎ በሥፍራው የነበሩት ስቲር የተባሉት ጋዜጠኛ የምሥክር ቃላቸውን ሰጥተዋል::

ጀግናው በተወለዱ በ30 ዓመታቸው አረፉ::ጠላትም እፎይታ አገኘ:: ወታደሮቻቸውም እምባ በእምባ ተራጭተው ቀበሯቸው::

ግራዝማች አፈወርቅ መስዋዕት በሆኑ በ14ኛው ቀን ከግርማዊ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የደጃዝማችነት መዕረግ ተሰጣቸው:: ለዚህም ክብር የበቁ የመጀመሪያው ጀግና ኢትዮጵያዊ ነበሩ::

ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ ያዘመቱት የጦር አውሮፕላኖች ብዛት 300 እንደሚደርስ ተዘግቧል::  396 ቶን ፈንጂዎች እንዳርከፈከፉም ይገመታል::

በደቡብ ምሥራቅ በኩል በኢትዮጵያ ላይ ለዘመተው የጠላት ጦር እንዲመክቱ ሦስት የጦር አለቆች ተሰይመው ነበር፡፡ ሦስቱንም አጠቃሎ የሚያዝና የሚያስተባብር የበላይ የሆነ ሳይኖራቸው ሦስቱም እራሳቸውን ችለው የበላይ አዛዥ ሆነው ነበር የዘመቱት፡፡ እነሱም፤

1.ራስ ደስታ ዳምጠው

2.ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኑኤል

3.ደጃዝማች በየነ መርዕድ ነበሩ::  ስለሆነም በአንድ ዕቅድና በአንድ አዛዥ ሥር አለመዝመታቸው ለጠላት ምቹ አጋጣሚን ፈጥረውለት እንደነበር ጥርጥር የለውም::  ጀግናው የኢዮጵያ ጦር እጅግ በአረጀ  የጦር መሣሪያ በመጠቀም  ከጣሊያን አገር በመርከብ ተጭኖ ከመጣው ሠራዊት ውስጥ ወደ 10,000  የሚጠጋው  የጣሊያን የጦር ሀይል አባሎች ተደምስሰዋል ተብሎ ተግምቱዋል፡፡

ራስ ሙሉጌታ በጊዜው የጦር ሚኒስትር እንደመሆናቸው መጠን ከሌሎች የጦር   ክፍሎች ጋር የሚገናኙበት ሬዲዮ እንኳን   እንዳልነበራቸው ተዘግቧል::

የኢትዮጵያ ጦር የወራሪውን የጣሊያን ጦር ለብዙ ጊዜ መክቶ ይይዛል ተብሎ ሲጠበቅ በ7 ወሩ ድል ሆነ::  ጄኔራል ባዶሊዎ የኢዮጵያዊያንን አልበገር ባይነትና የተፈጥሮ ጀግንነትን ሳይክድ መስክሮዋል::   ለኢትዮጵያ ጦር መሸነፍ ዋናው ምክንያት ነው ብሎ ቃሉን የሰጠው የጦር አዝማቾቹ ዘመናዊ የጦር ውጊያ አመራር ችሎታ ስለጎደላቸው ነበር ብሏል:: ይህ ትልቁ ችግር ቢሆንም ዘመናዊ መሣሪያ አለመታጠቁ ከዋና ጉድለቶቹ አንዱ ለመሆኑ ሁሉም የሚስማማበት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ጦር በሰሜንም ሆነ በደቡብ ያለው ሠራዊት ተበታትኖ የሠፈረና በመገናኛ መስመር የማይገናኝ ከመሆኑም በላይ ጠቅላይ እዝ የሌለው ነበር:: ሽንፈት ሲገጥመውና ማፈግፈግ ሲኖርበት ተጠባባቂ ጦር የሌለው ነበር::

የጣሊያኑ ጦር አዛዥ ጄኔራል ባዶሊዎ ጦሩን ይዞ ማክሰኞ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ ም አዲስ አበባ ገባ::ሙሶሊኒም ምኞት ስልተሳካለት በይፋ ፈነጠዘ:: ሕይወታቸውን መስዋዕት ላደረጉ አርበኞቻችን ክብርና ሞገስ ይድረሳቸውና ፍልሚያው ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ሄዶ የግራዝማች አፈወርቅንና የልሎቹንም ፈር ቀዳጅ አረበኞች ተክተለው ለአምስት ዓመታት በዱር በገደሉ የአርበኞች ትግል ተካሂዶ በጠላታችን ላይ ድልን ለመጎናጸፍ ቻልን::

እንደ ጀግናው ደጃዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማያት ያሉ ግምባር ቀደም አርበኞች ምሥጋና ይግባቸውና በዚያ በጎልማሳ እድሜያቸው ለአገራቸው ሕይዋታቸውን መስዋዕት ያደረጉ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጆችን በመከተል በሺ የሚቆጠሩ አርበኞች ተፈጥረው በመዋጋታቸው የነፃነታችን ችቦ እንድገና በመላ ኢትዮጵያ ቦግ ብሎ ሊያበራ ችሉዋል ::

ደጃዝማች አፈወርቅ ያን አነስተኛ ሠራዊት ይዘው ዘመኑ ባለፈበት መሣሪያ ተጠቅመው እመክታለሁ ማለታቸው ለአገር ያላቸውን ወደር የሌለው ፍቅር በማንፀባረቅ መስዋእት ሆኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ገድል ዘርግቶ እንደማለፍ የሚቆጠር ነው ::

በቆራጥ የአመራር ብቃታቸውና የከፈሉትን መስዋቅትነት በመገንዘብ በጂጂጋ በግርማዊ ቀዳማዊ ሀይለሥላሴ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ አንድ ትምህርት ቤትና አንድ ሆስፒታል በደጃዝማች አፈወርቅ ስም እንዲሰየምና በቆራሂ ላይ ደግሞ ምስላቸውን በያዘ ቅርፅ ሃውልት ተሠርቶ ንጉሰ ነገሥቱ በተገኙበት እንዲመረቅ ተደርጓል::

ከዚህም በተጨማሪ በወታደራዊው "ደርግ" ዘመነ መንግስት በጂጂጋ ከተማ ሀውልት እንዲቆምላቸው ተደርጓል::

ቆራሂ የነበረው ሀውልታቸው በፀረ ህዝብና በፀረ እንድነት ሀይሎች መፍረሱ በወቅቱ ለነፃነትና ለአገር ክብረ ተቆርቋሪ የሆነውን የኢትዮጵያን ህዝብ እጅግ እንዳስቆጣው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው:: የአገር ወዳዱ ሰላማዊ ህዝብ ትግል ይህን አሳፋሪ ድርጊት በትግሉ ግዜውን ጠብቆ ያስተካክለዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን_::



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በኦጋዴን የደጃዝማች አፈወርቅን
የመቃብር ሀውልት ሲመርቁ

## ዋቢ መጽሐፎች

1. የኢትዮጵያ ታሪክ
   1. 1 ከዐፄ ንብለ ድግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ
   1. 2 ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ዐፄ ሀይለ ሥላሴ
   ከተክለ ጻዲቅ መኩሪያ
2. Cesar in Abyssinia, ከ G.L. Steer
3. የኢትዮጵያ አስተዳደርና ፖለቲካዊ ሂደት
   ከዮሐንስ መሸሻ
4. ቀሪን ገረመው: ከታደሰ ዘወልዴ
5. Empress Taytu and Menelik II
   ከChriss Prouty
6. The Campaign of Adwoa and the rise of Menelik II
   ከBerkeley G. F. H.
7. Abyssinia and Italy- An examination of the cause of the war
   Burns E.
8. የኢትዮጵያና የጣሊያን ጦርነት:ከጳውሎስ ኞኞ
9. የኢትዮጵያ አንድነትና እና ኢጣሊያ: ከዶክተር ተወልደ ትኩአ
10. የታሪክ ማስታወሻ:ከደጃዝማች ከበደ ተሳማ
11. Ethiopia at Bay, ከጆን ስፔንሰር (John Spencer)